# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)


## ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
## የቀረበ ዳግም ጥሪ

### <u>በግልጽ አጀንዳ፥ በግልጽ አካሄድ</u>

የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦት ወር ፲፱፻፺፯ ዓ/ም የምርጫ ሂደት ታግሎና ተሰውቶ የተጎናጸፋቸውን ድሎች ጥቂት የሥልጣን ጥመኞች ዓይልን ባወጣ መልክ ሊቀሙት የሚቻላቸውን ሁሉ መፈጸማቸውና አሁንም እያደረጉ መሆኑ ቢታወቅም ይኸንን የልጆቹን ክቡር መስዋዕትነት ፍሬ መልሶ እጁ ውስጥ ለማስገባት ካስፈለገ ተጨማሪ መስዋዕትነት እየከፈልኩም ቢሆን ተጋድሎየን እቀጥላለሁ፥ ታግላችሁ አታግሉኝ እያለ ሲወተውት እነሆ ወራት አስቆጥሯል። ይኸንን ሕዝባዊ ጥሪ እውን ለማድረግና አገራችን የተያያዘችው የዴሞክራሲ፥ የሰላምና የብሔራዊ እርቅ ሂደት ፈር ስቶ መልሰን አንቅረን ወደተፋነው የአፈና፥ የግፍና የቂም በቀል አዙሪት ውስጥ እንዳንዘፈቅ ቅንጅቱና ኅብረታችን ይኸንን የሕዝብ ጥሪ ሰምተው ለዚህ ተጋድሎ ተፈላጊውን አመራር ለመስጠት የማይታጠፍ ቃላቸውን በሰጡት መሠረት እስካሁን እየታገሉ በማታገል ላይ ናቸው። ሆኖም ጥቂት የኢሕአዴግ መሪዎች ለዚህ የማያወላውል የሕዝብ ፈቃድ ከመገዛት ይልቅ ለዚህ ሰማዕትና ታጋይ ሕዝብ ያላቸውን ከፍተኛ ንቀት ባጋለጠባቸው መልክ ከራሳቸው ሕገ-መንግሥት አንፃር እንኳ ጨርሶ ሕገ-ወጥ የሆነ የሌቦች ዋሻ ፓርላማቸውን መሥርተው፥ በዚህ ከጥንስሱ ሕገ-ወጥ በሆነ ስብስብ መንግሥት ለመመሥረት ሕገ-መንግሥታዊም፥ ፖለቲካዊም፥ ሕጋዊም ሆነ የሞራል ብቃት በሌለው ፓርላማ መንግሥት ሰየምን ብለው አገራችንን ለሌላ አምስት ዓመታት የግፍ አገዛዝ እያመቻቹ ይገኛሉ።

በኅብረታችን እምነት እነዚህ ጥቂቶች በዚህ ሕገ-ወጥ ጎዳና እንዲቀጥሉ ፈቅደንላቸው ከቀጠሉና የሕዝባችን ትግል ትጥቅ ከፈታ ግፈኛ አገዛዛቸው በአገራችን ላይ የመከራ ዘመኑን የሚያራዝመው ለቀጣዮቹ አምስት ዓመታት ብቻ አይሆንም። ይኸ ዛሬ በዓይናችን ሥር ተቀጣጥሎ የሕዝባችንን ድል ለማስከበር የሚካሄደው ተጋድሎ በጥቂት ሥልጣን ጥመኞች አመፅ ከተሸነፈና እኛም ይኸንን አመፅ አሁን በሰላማዊና በሕዝባዊ ክንድ ተቋቁመን ወደፊት ካልተራመድን የዛሬ አምስት ዓመት ወይም የዛሬ አሥር ዓመት ተንቀሳቅሰን ሕዝባችን ድል ቢያደርግ እንኳን እንደገና በአመፅ ድሉን ላለመቀማቱ ምንም ዋስትና ስለማይኖር አገራችን አሥርም ሃያም ዓመታት ወደ ኋላ ተጉዛ የመከራውና የግፉ ዘመን ለረጅም ጊዜ እንዲቀጥል ለሁላችንም ግልጽ መሆን ይኖርበታል።

በመሆኑም ከእንግዲህ ለሕዝባችን የሞት ሽረት የሆነው የግንቦት ድሎች መከበር ጉዳይ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የማንም ሳይሆን የሕዝባችን አንገብጋቢ ጉዳይ በመሆኑና ሕዝባችንም በዋና ባለጉዳይነት "ያገባኛል ልግባበት" እያለ የሚያስተጋባውን የ"ምሩኝ ልከተላችሁ" ጥሪ እኛ ታጋይ ኃይሎች ሰምተን ለዚሁ ምላሽ ሁኔታዎችን ስናመቻች ቆይተናል። በተደጋጋሚ ከሕዝባችንም፥ ከየድርጅቶቻችን አባላትና ደጋፊዎችም፥ ከጠቅላላው በውጭም በውስጥም ካሉ አገር-ወዳዶችና ዴሞክራቶችም የሚስተጋባውን ጥሪ በማዳመጥ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ አመራር ከጥቅምት ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም ጀምሮ በተከታታይ የሚደረጉ የሰላማዊ ተጋድሎ ስልቶች በዝርዝር ማቅረቡና ኅበረታችን በተለይ ከሦስት ሳምንታት ወዲህ ' "ዜጎች ለግንቦት ድሎች" ብለን እንሰባሰብ' በሚል ጥሪ ሕዝባችን የትግሉ አጋር ሆኖ፥ በአንድ መንፈስና በአዲስ ወኔ የተሰረቀ ድሉን ለማስከበር እንዲንቀሳቀስ ጥሪ ሲያደርግ የቆየበት ጉዳይ በመሆኑ ከቅንጅቱ ለቀረበው የሰላማዊ ትግል


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሳ.ቁ 18573 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
P.O.Box 18573 Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ ቁጥር/Tel. 251-1574719;ፋክስ/Fax:2511574720

ሰሜን አሜሪካ (North America)
P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
ስልክ/Tel. 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

ጥሪ ድጋፋችንንና ትብብራችንን መግለጻችንና በውስጥም በውጭም ያሉ አባላቱና ደጋፊዎቹ እንደዚሁም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይኽ የትግል ጥሪ የኅብረቱም የቅንጅቱም ሳይሆን ከራሳቸው ፍላጎትና ፈቃድ የመነጨ ጥሪ አድርገው በመቁጠር ለተግባራዊነቱ ከዳር እስከዳር እንዲንቀሳቀሱና ጥቂት የኢሕአዴግ መሪዎችና አንዳንድ ባዕዳን የተዘጋ የመሰላቸው የግንቦት ምዕራፍ ከመዘጋት ይልቅ ወደ ሌላ ከፍተኛ የትግል ምዕራፍ እየተሸጋገረ መሆኑን እንዲያሳዩ አገራዊ ጥሪያችንን ማስተላለፋችን ይታወቃል።

ምን ጊዜም አኩሪው ታጋይ ሕዝባችን ከአታጋይ ድርጅቶቹ ለሚቀርብለት ጥያቄና አስተማማኝ የትግል ጥሪ በተግባር መልስ ለመስጠት ያለውን ዝግጁነትና ቁርጠኝነት የተመለከተውና በዚህ አልበገር ባይ የሕዝብ ማዕበል የራደውና የተርበተበተው የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ አሁንም ተሸቀዳድሞ የፈሪ ዱላውን በንጹሐን ዜጎች ላይ አወረደው። የድርጅት መሪዎችን፥ የነፃው ጋዜጣ አዘጋጆዎችን፥ የቀድሞ ሠራዊት አባላትን፥ ወጣት፥ ባልቴት፥ አዛውንት፥ ሳይለይ ሰላማዊ ዜጎችን በገፍና በግፍ አሰረ፥ አንገላታ። ብዙ ንፁኃን ዜጎችን ባዕዳን እንኳን ያደርጉታል ተብሎ በማይጠበቅ አረመኔአዊ ሁኔታ ጨፈጨፈ።

የሕዝብን ዴሞክራሲያዊና ፍትኃዊ የምርጫ ፍርድ ለመቀበል የተናነቀው ይኽ አገዛዝ ምርጫውን ለመስረቅ ከወሰነ ጊዜ ጀምሮ ተቃዋሚውን ክፍል በመወከል ለሕዝብ ተወካዮችና ለክልል ምክር ቤቶች በተወዳደሩ ታጋዮች፥ የድርጅት አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ድምፃቸውን ለተቃዋሚው በሰጡ ብቻ ሳይሆን በግልጽ ከገዥው ፓርቲ ባልወገኑ ንጹኃን ዜጎች ላይ እንግልት፥ እስራት፥ ግድያ፥ ዘረፋ፥ በዓይን ውስጥ በርበሬ እየጨመሩ ዘቅዝቆ ሰቅሎ መግረፍ፥ ሰው ላይ ጭድ ነስንሶ በእሳት ማቃጠል፥ ወዘተ.... በአጠቃላይ ይኽ ነው የማይባል ግፍ ሲፈፈጸም ቆይቷል። አሁንም አገዛዙ በዜጎች ላይ በአወጀውና በአፋፋመው አዲስ ዙር የሽብር ዘመቻ ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ዜጎችን፥ በአብዛኛው ወጣቶችን፥ አፍሶ በረሃ ላይ እንዳፈሰሳቸውና ማን የት እንዳለ መታወቅ በማይቻልበት አሳዛኝ ሁኔታ ላይ እንደሆኑ እየተገለጸ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) በአገዛዙ አረመኔአዊ የኃይልና የጉልበት እርምጃ በግፍ ሕይወታቸውን ላጡ ዜጎች ቤተሰቦች ሁሉ ከልብ የመነጨ ሃዘኑን ይገልጻል። በአረመኔዎች እጅ የወደቁት ልጆቻቸው፥ አባት፥ እናት፥ እህት፥ ወንድሞቻቸው ሁሉ ምንም አጥፍተው እንዳልሆነ ይታወቃል። የእነኝህ ንጹኃን ዜጎች ደም ነገ በአገራችን ላይ እንደዚህ ዓይነት ግፍ እንዳይደገም፥ በብሔራዊ መግባባትና እርቅ ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲኖር ማስቻል ይኖርበታል። በዚህ የሕዝብ መብት የማስከበር ፍትኃዊና ሰላማዊ ትግል የወደቁ ዜጎቻችን ምን ጊዜም ሲዘከሩ የሚኖሩ ሰማዕታት ናቸው።

የኢሕአዴግ መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ባወጀው በዚህ አዲስ ዙር የሽብር ዘመቻ ምክንያት የአገራችን ሁኔታ ወደባሰ አስከፊ ደረጃ ተሸጋግሯል።

ስለሆነም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት፤

1. የኢሕአዴግ መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያወጀው የሽብር ጦርነት ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲቆምና ከመደበኛ ሰላማዊ ፖሊስ ውጭ ያሉ አገዛዙ የገዛ ሕዝባቸውን እንዲያሰቃዩና እንዲጨፈጭፉ ያሰማራቸው ልዩና የመደበኛው ጦር ክፍሎች ወደ መደበኛና ሕጋዊ የጠረፍ ጥበቃ ሥራቸውና ወደየጦር ሠፈራቸው እንዲመለሱ ፤

2. ያለ ምንም ጥፋት በግፍ የታሰሩ የድርጅት መሪዎች፥ የነፃው ጋዜጣ አሳታሚዎችና ጋዜጠኞች፥ ወጣቶች፥ በአጠቃላይ በዚህ አዲስ ዙር የሽብር ዘመቻ የታፈሱ ሁሉ ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈቱ፤

3. በዚህ አዲስ ዙር የሽብር ዘመቻና በሰኔ ወር ፲፱፻፺፯ ዓ/ም በተመሳሳይ ሁኔታ አገዛዙ በወሰደው የግፍ እርምጃ በሕይዎትና በአካል ላይ የደረሰውን ጥፋትና ወንጀል የሚያጣራ ገለልተኛ አካል በአስቸኳይ እንዲቋቋም፤ ጥፋተኞች ለፍርድ እንዲቀርቡ እንዲደረግና ለተጎጅዎች አስፈላጊው ካሣ እንዲከፈል፤

4. በኢሕአዴግ የሚመራው የአቶ መለስ ዜናዊ መንግሥት አገራችን አሁን እንድትገኝ ባደረጉበት እጅግ አሳፋሪና ውስብስብ ሁኔታ ኢሕአዴግም በሰላም ለመግዛት እንደማይችል የኢትዮጵያ ሕዝብም የፈለገው ዓይነት ግፍ ቢደርስበት ዝም ብሎ እንደማይገዛና እንኳን አሁን አዳዲስ ግፎች ተፈጽመውበት ቀርቶ በፊትም ቢሆን ወደ መርጫ ጨዋታ ሲገባ በሙሉ ቁርጠኝነትና ወሳኝነት አንቅሮ ወደተፋው አስከፊ የአሥራ አራት ዓመት ይዞታው ላለመመለስ መሆኑ በተገቢ ግልጽ ሊሆን ይገባል። ስለሆነም ከአሁን በፊትም እንዳቀረብነው ሁሉ የአገር-በቀልና የውጭ ታዛቢዎች በሚገኙበት የፖለቲካ ድርጅቶች፥ የሲቪክና የሙያ ማኅበራት ተወካዮች፥ አገር-ወዳድ ምሁራን፥ ወዘተ ... የሚሳተፉበት አንድ ሁሉን አቀፍ አገራዊ ጉባዔ በአስቸኳይ እንዲጠራና በአገሪቱ ሁኔታ ላይ ተወያይቶ ቀደም ሲል ቅንጅቱና ኅብረቱ ባቀረቡት የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ማቋቋም መንፈስ የጋራና ለሁሉም የሚጠቅም መፍትሔ እንዲሻ፤
ይጠይቃል።

ለዚህና ሕዝቡ ለተነሳበት የድምፅ መከበር መሠረታዊ ዓላማ እውን መሆን አንዴ እርባና በሌለውና ቀናነት በጎደለው የብልጣ ብልጥ ድርድር ተብየ ቧልት፥ ሌላ ጊዜ ይኸ የሌቦች ዋሻ ወደሆነ ፓርላማ መግባት አለመግባት በሚል ጨዋታ ሳይዘናጋና በተናጠል እየተነሳ በተናጠል እየተመታ ትግሉ የመቀልበስ አደጋ ደርሶበት ፍጹም የለየለት አምባ-ገነን አገዛዝ በአገራችን እንዲሰፍን የሚያደርግ አደገኛ ሁኔታ እንዳይገጥም መዋዠቅ ሳይኖር በጠራና ግልጽ በሆነ የትግል መስመር ሕዝባችን የተያያዘውን ሰላማዊ ትግል መቀጠል ይኖርበታል። ድርጅቶቹም የጠራ መሥመር የተከተለ ግልጽ አመራር መስጠት ይጠበቅብናል።

ሕዝባችንን ይዘንና በሕዝባችን ታቅፈን የምንያያዘው አዲስ የትግል ምዕራፍ ዓላማውና ስልቱ ግልጽ ነው። ሕዝባችን በዚህ አዲስ ምዕራፍ የሚጠበቅበትን መስዋዕትነት ለመክፈል ቆርጦ የሚነሳሳው የተነጠቀ የግንቦት ድሎቹን መልሶ እጁ ውስጥ ለማስገባት ነው። ይኸንን የሚያደርገው ደግሞ ወይ በአጠቃላይ የግንቦቱ ምርጫ ሂደት በአዲስ መልክ በተዋቀረ ሁሉም ወገኖች በተስማሙበት ገለልተኛ አካል ሲገመገም ወይም ደግሞ ሌላው ቀርቶ ዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብም ለመጭበርበሩ የምስክር ቃል የሰጠበት ምርጫ በሌላና ሁሉም በተማማበት የምርጫ ቦርድ፥ በሌላና ዴሞክራሲ በሰፈነበት ሁኔታ ሲደገም ብቻ ነው።

ባለፉት ስድስት ወራት የኢሕአዴግን መሪዎች የሕዝብ ድምፅ አክብሩ እያልን ስንጮህ በእኛ በኩል የሕዝብ ድምፅ አለማዳመጣችን የማይታሰብ ጉዳይ ስለሆነ፥ የኢሕአዴግ መሪዎችን ባለፉት ስድስት ወራት የፈሰሰውን የልጆቻችንን ደምና የወላጅ እንባ እንደ ቀጭን ውሃ ቆጥራችሁ አታዋርዱት እያልን እየተሟገትናቸው እኛ “የሕዝብ ድምፅ ይከበር” እያሉ የወደቁትን ዜጎች ሰማዕትነት አለማክበራችን የማይታለም ጉዳይ በመሆኑ፥ የኢሕአዴግ መሪዎች በውጭም በውስጥም የሕዝብ ድምፅ ይከበር ብለው ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ዜጎች የሚያካሂዱትን ተጋድሎ ሚዛን የማይደፋና የትም የማያደርስ የጥቂቶች መፍጨርጨር አድርገው ሲንቁት እኛ ለዚህ ለሕዝባዊ ማዕበል ጆሮ ዳባ ልበስ የምንልበት የታጋዮች ንቀት ባህል ስለሌለን ከዚህ የሕዝብ ድምፅ ከማስከበር በመለስ የምንረካበት ምንም ዓይነት ድል እንደማይኖር ለሚመለከተው ሁሉ ከወዲሁ ግልፅ መሆን ይኖርበታል።

የትግል ስልታችንም ከዚህ ዘላቂና ሕዝባዊ ዓላማ ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው። ዓላማችን የኢሕአዴግ መሪዎች የሕዝቡ ድምፅ ስለሚከበርበት ሁኔታ ትርጉም ወዳለው ድርድር እንዲመጡና ለእኛም፥ ለነሱም ለሕዝባችንም የሚበጅ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ

መፍትሔ ላይ ለመድረስ ነው:: ከዚህ በመለስ የምንደራደርበት ጉዳይ ሊኖር አይችልም:: በሕዝብና በዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብ ግፊት የድርድርን አሳብ ከተቀበሉ መጀመሪያ ነገር የድርድሩ አጀንዳ በቅድሚያ ለሕዝብና በአገሪቱ ላሉ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች በሙሉ በግልጽና በይፋ መቀመጥ ይኖርበታል:: ሁለተኛ ነገር ይኸ የድርድር ጥሪ ወይም ፍላጎት የሕዝባችንን ትግልና እንቅስቃሴ የሚተካ መሆን የለበትም:: የፀረ-ሕዝብ ተንኮል ቋት የሆኑት የኢሕአዴግ መሪዎች ሲያመቻቸው በጠብ-መንጃ አመፅ ሳያመቻቸው በመለሳለስ የሕዝቡን ትግል ለማደናገርና ለማሰናከል ስለማይመለሱ ከወዲሁ አንድ ነገር ግልፅ ሆኖ መቀመጥ ይኖርበታል:: ከእንግዲህ ማንኛውም ድርድር ኅብረተሰቡን ከዳር እስከዳር አንቀሳቅሶ፥ ሕዝባችን ከመሪዎቻችን ጀርባ በተጠንቀቅ ቆሞ ብቻ መሆን ይኖርበታል:: በየጊዜው ለሕዝብ የምናቀርባቸው የትግል ጥሪዎች ግልጽ፥ የሕዝቡን አቅምና ሁኔታ ያገናዘቡ፥ ተፈጻሚነት ያላቸው፥ ከሁኔታውና ከጊዜው ጋር የሚጣጣሙና ወቅታዊ የሆኑና በተከታታይ ሊቀርቡ የሚችሉ ተለዋጭ ስልቶችን ያጣጣመ፥ ወዘተ... መሆን ይኖርባቸዋል:: በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደማናቸውም ሰላም ወዳድና ለመብቱ መከበር የሚታገል ሕዝብ ሁሉ መሪዎቹ ሲታሰሩበት፥ ልሳኖቹ ሲዘጉበት፥ ዜጎች በዘፈቀደ ከየቤታቸው እየተወሰዱ ሲታረዱበት፥ ወጣቱ ከየሰፈሩ እየታፈሰ የትም ሲጣልበት፥ ወዘተ... ቋሚ ዒላማ የሚያደርገውና ተነጥሎ የሚጠቃበት ሁኔታን ማስወገድና ለእንደዚህ ዓይነት ግፍ አመች ሆኖ እንዳይገኝ ሕዝባችን ከዳር እስከ ዳር እንደ አንድ ሰው ሆኖ እንዲነሳና ለአመፀኛው አገዛዝ ምንም ፋታ በማይሰጥ ሁኔታ ትኩስ እንቅስቃሴ የሚያደርግበት ስልት ተቀይሶ ጥሪ ሊቀርብለት ይገባል:: ከአሁን በፊት እንደገለጽነው ሁሉ አሁንም ኅብረቱ ከሌሎች አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች፥ የሲቪክና የሙያ ማኅበራት ጋር በመሆን ተከታታይ የትግል ጥሪዎችን እንደሚያቀርብ እናስታውቃለን::

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች (ኢዴኃኅ) ከነዚህ ነጥቦች በመነሳትና ለነዚህ ዓላማዎች መሳካት አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች፥ የሲቪክና የሙያ ማኅበራት፥ ስብስቦች፥ ወዘተ... ይኸንን ሰላማዊና ፍትኃዊ የሕዝብ ትግል በጋራ በመቆም ሕዝባችንን እየደረሰበት ካለው ቀጣይ ግፍ፥ ስቃይና መከራ እንድንገላግለው አበክረን እንጠይቃለን፥ የትብብር ጥሪም እነሆ እናቀርባለን::

የሕዝባችንን ድምፅ ለማስከበር በመዋደቅ ላይ የሚገኙ በውጭ የሚገኙ ስብስቦችም ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በሰላማዊ ሰልፎችና በሌሎች የትግል ስልቶች አማካይነት የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች ይበልጥ እንዲያጠናክሩ፤ መጭው ውስብስብ ትግል በአገር ውስጥ ለሚዋደቁ ዜጎች ከፍተኛ የገንዘብና የማቴሪያል አቅም ስለሚጠይቅ በያለበት በተቋቋሙ የድጋፍ ኮሚቴዎች አማካይነት የገንዘብ እርዳታ ስብስባ ዘመቻ እንዲካሄድ ጥሪ እያቀረብን የኅብረቱ አባላት፥ የድጋፍ ኮሚቴዎችና ደጋፊዎች በያሉበት ለዚህ የጋራ ትግል መሳካት የሚያደርጉትን ጥረት ከእስካሁኑ በላቀ መልኩ በማድረግ “የግንቦት ምዕራፍ አልተዘጋም፥ አይዘጋም” ብለን ላስተላለፍነው ጥሪ ተግባራዊነት እንዲረባረቡ አገራዊ ጥሪያችንን ከአክብሮት ጋር እናስተላልፋለን::

ኢሕአዴግ በኢትዮጱያ ሕዝብ ላይ ያወጀው ሽብር በአስቸኳይ ይቁም!
የታሰሩ  ዜጎች ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ በአስቸኳይ ይፈቱ!!
የግንቦት ድሎች በዜጎች የጋራ ተጋድሎ ይከበራሉ!!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት
ኅዳር ፫ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም